ፋብሪካችን ሞሓ የለስላሳ መጠጦች ኢንዳስትሪ አክስዩን ማህበር መቐለ ፋብሪካ ለፋብሪካው ኣገልግሎት የሚውል የተለያዩ ዓይነት የላብራቶሪ ዕቃዎች እና ኬምካሎች በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

- የተለቀቀበት ቀን: ሶኒ ሕዳር 17, 2011 (ከ 8 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: ታሕሳስ 1, 2011 8:15 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:2%
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:30.00
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ታሕሳስ 1, 2011 8:30 ጥዋት
- ምድብ: ኬሚካልን ሪኤጀንት/ ላብራቶሪይን መሳሪሒታተ/

ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለፁትን መምርያ ኣክብራችሁ መወዳደር የምትችሉ ተጫራቾች ሁሉ መጫረት የምትችሉ መሆኑ በኣክብሮት እንገልፃለን።

የጨረታ መምርያ

1 ተጫራቾች በዘርፉ የዘመኑ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ : የኣቅራቢነት ምዝገባ ሰርተፊኬት: የቫት ተመዝጋቢ መሆኑ የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት እና ቲን ምዝገባ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2 ተጫራቾች ለጨረታዉ ማስከበሪያ የጠቅላላ የጨረታ ዋጋ 2% የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ CPO ማስያዝ ይኖርባቸዋል ።

3 ተጫራቾች የሚቀርቡትን ዋጋ ቫት ያካተተ ሙሆኑን እና አለመሆኑን በግልፅ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን ዋጋዉ ቫትን ያካተተ መሆኑ ታሳቢ ይደረጋል።

4 ተጫራቾች ኣሸናፊ ከሆኑ እቃው የሚያቀርቡበትን ግዜ፣ የመረካከብያ ቦታ እና ዋጋው የሚፀናበት ግዜ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።

5 የጨረታዉ ዝርዝር ሰነድ ከድርጅቱ ፋይናንስ መምሪያ ቢሮ ቁጥር 15 ድረስ በመምጣት እና የማይመለስ ብር 30.00 በመክፈል መውሰድ ይቻላል።

6 በጨረታ ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ ተቀባይነት ኣይኖረዉም።

7 ተጫረቾች ዋጋቸዉ በታሸገ ኢንቨሎፕ ይህን ጨረታ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ እስክ ከ 01/04/2011 ዓ/ም በስራ ቀንና ሰዓት ኣክሱም ሆቴል ፊት ለፊት ከሚገኘዉ ዋና ቢሮኣችን ድረስ በመምጣት ለዚሁ ተብሎ በተዘገጀዉ የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ የጨረታ ሰነድ እና የሰነዱ ማሸግያ ፖስታ ተጫራቾች ህጋዊ ማህተምና እና ፊርማ መኖር ይኖርበታል።

8 የጨረታ ሳጥኑ ጥቅምት 01/04/2011 ዓ/ም ከቀኑ 8:15 የሚታሸግ ሲሆን ከዚሁ ሰዓት ባኃላ የጨረታ ሰነድ የሚመጣ ተቀባይነት ኣይኖረዉም።

9 ጨረታዉ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት/ ባልተገኙበትም 01/04/2011 ዓ/ም ከቀኑ ልክ 8:30 በፋብሪካዉ የግዥና ክምችት መምሪያ ቢሮ ወስጥ ይከፈታል።

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

10 ተጫራቾች በዚህ ጨረታ ላይ ያሸነፈቸዉን የእቃ አይነቶች ማሸነፋቸዉ እንደተነገራቸዉ በ7 ቀናት ወስጥ እቃዎችን የማስረከብ ግዴታ ይኖርባቸዋል።ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን ያስያዘዉ የዉል የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ ካለ ምንም ቅድመ ሆኔታ ለድርጅቱ ገቢ ይሆናል።

11 ማንኛዉም ተጫራች ጨረታዉ ከተከፈተ ባኃላ ጨረታዉን መሰረዝ ኣይችልም።

12 ስርዝ ድልዝ የሆነ የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረዉም።

13 ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ በማንኛዉም ግዜ ጨረታዉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ።

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle